# የተማሪዎች አደባባይ ድምፅ ማሰሚያው ጊዜ አሁን ነው !!!!

በዛሬው ቀን የጀርመን አማርኛ ዘገባ በ ወልደያ የሚገኙ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በወልደያ ዩኒቨርስቲ በጎሣ ጥቃት ለተገደሉት ሁለት ተማሪዎች ና አካል ጉዳት ከደረሰባቸው ጎን በመቆም የ አደባባይ ሰልፍ ማድረጋቸው በ መላ ኢትዮጵያ ለሚገኙ ተማሪዎች ታላቅ ምሳሌ ነው።

በተቃራኒው የ ኦሮሞ ፓርቲዎች በኦሮሞ ክልል ባለፈው ሳምንት 86 ንፁሀን ዜጎችን ህይወት የነጠቀ ከፍተኛ መፈናቀል ቤተክርስቲያናት መስጊድ ንግድ መኖርያ ላይ የደረሰውን አደጋ ላይ መግለጫ ለመስጠት ያልፈጠኑ ዛሬ የወልደያ ዩኒቨርስቲ ህይወት ጥፋት ወደ ሌላ ጎሣ ግጭት የሚጋብዝ መግለጫ ሰጥተዋል።

በዶምቢዶሎ ዛሬ አንድ ዩኒቨርስቲ ተማሪ ላይ የጎሣ ግድያ መፈፀሙን በ አለም ማያ ና ሌሎች ዩኒቨርስቲዎች ዉጥረት መኖሩንም ሰምተናል ።

የወልደያ ተማሪዎችን አርአያነት በመከተል በመላው ኢትዮጵያ አደባባይ በመዉጣት መማሪያ ቦታዎች ውስጥ በመፈፀም ላይ ያለዉን የጎሣ ግድያዎችን በማውገዝ ድምፃቸውን ማሰሚያው ጊዜ አሁን ነው።

በተለይ የአዲስ አበባ ተማሪዎች መሬት ለአራሹ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት እያልን እየዘመርን ባደግንበት ከተማ ዝምታ በአሁኑ ሰዐት  እጅግ ያሳዝናል።

ወጣቶችን በጎሣ ለይቶ በየዩኒቨርስቲዎች ለማጋደል በሚሰራበት አገር ዝም የሚል ወጣት ሊፈጠር አይገባም።

ወጣቶች በ ኮሌጅና ዩኒቨርስቲዎች  የተማሪዎች ህልውና ጥያቄ በማንሣት አደባባይ ድምፅ እንዲያሰሙ ወላጆችም ድጋፍ ልንሰጣቸው ይገባል።

ወላጆችም በመሰባሰብ የልጆቻቸውን ደህንነትየኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት እንዲያስጠብቅ ድምፃቸውን ማሰሚያው ጊዜ ዛሬ መሆኑን ተገንዝበው መነቃነቅ ይኖርባቸዋል።

**Tedla Asfaw**

**12/11/2019**